# በኢንዲያናፖሊስ ፅጋ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን

## የዮሐንስ ወንጌል ጥናት

/ክፍል አንድ/


አዘጋጅ

መጋቢ ዮሴፍ ደስታ

# የዮሐንስ ወንጌል ጥናት

## ማውጫ

1. የመግቢያ ሃሳቦች ስለ ዮሐንስ ወንጌል መፅሐፍ
    1.1 መፅሐፉ የተጻፈበት ዓላማ ምንድነው?
    1.2 በማን ተጻፈ?
    1.3 መቼ ተጻፈ?
    1.4 ከየት ተጻፈ?
    1.5 ለማን ተጻፈ?
    1.6 የመጽሐፉ ዋና ዋና ሃሳቦች / Major Themes / ምንድናቸው?
    1.7 የዮሐንስ ወንጌል ከሌሎቹ ሶስት ወንጌላት /Synoptic gospels / የሚለየው በምንድነው?
    1.8 የመጽሐፉ ማውጫ
2. የዚህ ጥናት ዓላማው ምንድነው?
3. ጥናቱ የተዘጋጀው ለማን ነው?
4. የአጠናን ዘዴ
5. ጥናቱ በግምት የሚፈጀው ጊዜ
6. የዮሐንስ ወንጌልን ለማጥናት የሚረዱ ጥያቄዎች
7. References

# 1. የመግቢያ ሃሳቦች ስለ ዮሐንስ ወንጌል መፅሐፍ

## 1.1 መፅሐፉ የተጻፈበት አላማ ምንድነው ?

የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈበት አላማ ወንጌል የመስበክ / Evangelistic/ ብቻ ሳይሆን ሰዎች በጌታ ከማመን ባሻገር በእምነታቸው እንዲያድጉና እንዲጠነክሩ ነው፡፡ ለዚህም አላማ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ለዘመናት ሲጠበቅ የነበረው መሲሁና የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን መፅሐፉ በሚገባ ያስተምራል፡፡ ጌታ ኢየሱስ መሲሁና የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ለማሳየት የተመረጡ ሰባት ተአምራቶችን አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም ብዙ ምስክሮችን አቅርቧል፡፡ ለምሳሌ መጽሐፍት /scripture/ ፣ መጥምቁ ዮሐንስ ፣ ራሱ ጌታ ኢየሱስ ፣ እግዚአብሔር አብ ፣ የጌታ ኢየሱስ ስራ ፣ መንፈስ ቅዱስና ራሱ ሐዋርያው ዮሐንስ የጌታን መሲህነቱን ከሚመሰክሩት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

- የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈበት አላማ በምዕራፍ 20፡30-31 ላይ በግልፅ ተፅፎአል፡፡ "· · ·ነገር ግን ኢየሱስ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆነ ታምኑ ዘንድ አምናችሁም በስሙ ህይወት ይሆንላችሁ ዘንድ ይህ ተፅፎአል፡፡"
- ስለዚህ የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈበት ዋና አላማ ጌታ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስና /መሲሁ/ ከላይ የመጣው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በብዙ መንገድና ሁኔታዎች በማሳየት ያላመኑ ሰዎች እርሱን በማመንና በመቀበል የዘላለም ህይወት እንዲያገኙና እንዲሁም አማኞች ደግሞ በህይወታቸው እንዲያድጉና እንዲጠነክሩ ነው፡፡
- ይኸውም ፡-
    - ደህንነት ወይም የዘላለም ሕይወት የሚገኘው በኢየሱስ ክርስቶስ ብቻ መሆኑን ለማሳየት

- ኢየሱስ እርሱ የሰውን ስጋ ለብሶ የመጣው ፣ ከላይ ከሰማይ የወረደው ክርስቶስ መሆኑን ፣ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑንና ብቸኛው የዘላለም ህይወት ምንጭ መሆኑን ለማስተማር
- የሐጢአትን ምንነቱንና ትልቅነቱን /the reality and magnitude of sin/ በብዙ መንገድ በማሳየት ከሐጢአት ለመዳን ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር መደገፍና መታመን የሚገባ መሆኑን ለማስተማር ነው፡፡

- በዮሐንስ ወንጌል የተጠቀሱ ተአምራቶች ንግግሮች ወይም ማንኛውም ክስተቶች በሙሉ የጌታ ኢየሱስን ማንነት የሚገልጹ ናቸው፡፡ ስለዚህ ማንም ሰው የዮሐንስ ወንጌልን አጥንቶ የኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት በጥልቀት የማያውቅ ሰው ሊኖር አይችልም፡፡ በአጠቃላይ የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ማንነት በግልጽ ለማስተማር በአዲስ ኪዳን ከተጻፉ መጽሐፍቶች ሁሉ በተለየ መንገድና በጥልቀት የተጻፈ መጽሐፍ ነው፡፡

## 1.2 <u>በማን ተጻፈ?</u>

- የዮሐንስ ወንጌልን በሚገባ በማጥናት /Internal Evidence/ ፀሐፊው

1. **<u>አይሁዳዊ መሆኑን ልናውቅ እንችላለን</u>**

- ይህንንም የምናውቀው ከአጻጻፍ ስልቱ፣ ስለብሉይ ኪዳን ካለው እውቀት፣ ስለመሲሁ ካለው እውቀት፣ ፀሐፊው በወቅቱ ከነበረው የአይሁድ ፖለቲካ ጋር የተሳሰረ በመሆኑ፣ የአይሁድን የሰርግና የቀብር ባህሎች በሚገባ የሚያውቅ መሆኑ ፀሐፊው <u>አይሁዳዊ</u> መሆኑን ያመለክታል፡፡

2. **<u>በፍልስጤም የሚኖር አይሁዳዊ መሆኑን እናውቃለን</u>**

- ይህንንም የምናውቀው ፀሐፊው የአካባቢውን መልክአምድር /topography/ በሚገባና በጥልቀት የሚያውቅ ስለሆነ ነው፡፡ ይህም ኢየሩሳሌም አካባቢውንና ቤተመቅደሱን ጨምሮ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ፀሐፊው <u>በፍልስጤም የሚኖር አይሁዳዊ</u> ነው ማለት ነው፡፡

3. **<u>የአይን ምስክር ነው</u>**

- ይህንንም ማወቅ የምንችለው በወንጌሉ የተከሰቱትን ክስተቶች በሚገባ ከማስታወሱም በላይ አንዳንድ ጊዜ ሰአት ሳይቀር በመጥቀሱ ነው ስለዚህ ፀሐፊው <u>የአይን ምስክር</u> ነው ማለት ነው፡፡

4. **<u>ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ነው</u>**

- የጌታን ራት አብሮ መቁረሱ ከአስራሁለቱ አንዱ መሆኑን ያሳያል /13፡23/ ከጴጥሮስ ጋር ያለው የቀረበ ግንኙነትና በወንጌሉ የተጠቀሱ ክስተቶችን ንግግሮችና ስሜቶች በጥልቀት ማወቁ <u>ከአስራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ</u> ነው ማለት ነው፡፡

5. **<u>ሐዋርያው ዮሐንስ ነው</u>**

- መፅሐፉን በሚገባ በማጥናት ሌሎቹ አስራ አንዱ አለመሆናቸውንና የዚህ መፅሐፍ ፀሐፊ <u>ሐዋርያው ዮሐንስ</u> መሆኑን ልንረዳ እንችላለን፡፡
- በሁለተኛው ሴንቸሪ ይኖር የነበረው አይረናይስ /Irenaeus/ የተባለው የቤተክርስቲያን አባትና ፖሊካርፕ /polycarp/ ከተባለውና በ155 AD መስዋዕት ሆኖ ከተሰዋው ሌላ ቀደምት የቤተክርስቲያን አባት ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበረው ሰው የዮሐንስ ወንጌል የተጻፈው በሐዋርያው ዮሐንስ መሆኑን ጽፎልናል፡፡
- ስለዚህ የዚህ መፅሐፍ ፀሐፊ ሐዋርያው ዮሐንስ መሆኑን ከራሱ ከመጽሐፉም /Internal evidence/ ከመጽሐፉም ውጪም /external evidence/ ማረጋገጥ ይቻላል ማለት ነው፡፡
- ሐዋርያው ዮሐንስ ማን ነው ?
    - የያዕቆብ ታናሽ ወንድምና የዘብድዮስ ልጅ ነው
    - የነጎድጓድ ልጆች ከተባሉት አንዱ ነው /ማር 3፡17/
    - እናቱ ሰሎሜ ትባላለች /ማቴ 27፡55-56፣ ማር 15፡40/

- በቅድሚያ ጌታ ከጠራቸው ቀዳሚ ሁለት ደቀመዛሙርት አንዱ ነበር /1፡35 ፣ 1፡40/
- በጌታ የስጋ ህይወት ወቅት የነበረና /contemporary/ የአይን እማኝ /eye witness / ነው። /21፡24፣ 1ኛ ዮሐ 1፡1-4/
- ስሙ ያልተጠቀሰው ደቀመዝሙር ነበር /1፡35፣ 1፡40፣ 21፡24/
- ኢየሱስ ይወደው የነበረ ደቀመዝሙር ነበር /13፡23/
- ኢየሱስን በሚገባ የሚያውቅ ደቀመዝሙር ነበር / 13፡25፣ 19፡26፣ 20፡8/
- በሰማርያ መንደሮች ላይ እሳት ከሰማይ ይውረድ ብለው ጌታን ከጠየቁት አንዱ ነበር /ሉቃስ 9፡51-58/
- አንድ ሰው አጋንንት ሲያወጣ አይተው ከከለከሉት አንዱ ነበር /ሊቃስ 9፡49-50/
- ሐይለኛ ብቻ ሳይሆን ራሱንም የሚወድ ነበር / ማር 10፡35-44/
- ኢየሱስ ወደ ራሱ ካቀረባቸው ሶስት ሐዋርያት /Inner circle/ አንዱ ነበር። /ማር 9፡2-13/
- ጌታ ሲሰቀል የነበረ ብቸኛው ደቀመዝሙር ነበር።
- ጌታ ሲሰቀል እናቱን እንዲጠብቅ አደራ የተሰጠው ነበር /19፡26-27/

- ምንም እንኳን የዚህ መፅሐፍ ፀሐፊ ሐዋርያው ዮሐንስ ቢሆንም ዋናው ደራሲ ዘላለማዊውን ሁሉ የሚያውቅና የሚያይ እግዚአብሔር ራሱ ነው። ሆኖም እግዚአብሔር ዮሐንስን ባህሉን ፣ ቋንቋውን፣ ጥንካሬውን፣ ድካሙን፣ ሁሉ ተጠቅሞ በሐዋርያው በኩል መልእክቱን አስተላለፈልን ። ስለዚህ ዮሐንስ ሙሉ በሙሉ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ስር በመሆንና በመንፈስ ቅዱስ በመነዳት /2ኛ ጴጥ 1፡25/ ወንጌሉን ጻፈልን።

## 1.3 መቼ ተፃፈ?

- ሐዋርያው ዮሐንስ የዮሐንስ ወንጌልን የጻፈው በህይወቱ ማብቂያ አካባቢ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ይኸውም ከ85-90 A.D. አካባቢ ማለት ነው፡፡ ይህም ማለት ከኢየሩሳሌም መፍረስ /70 A.D./ በኂላና ሐዋርያው ፍጥሞ ወደተባለች ደሴት ተይዞ ከመወሰዱ በፊት ማለት ነው፡፡

## 1.4 <u>ከየት ተጻፈ?</u>

- መጽሐፉን ሐዋርያው ዮሐንስ ኤፌሶን ሆኖ እንደጻፈው ይታመናል፡፡

## 1.5 <u>ለማን ተጻፈ?</u>

- የዮሐንስ ወንጌል ምንም እንኳን በእግዚአብሔር ዘላለማዊ አሳብ በዘመናት ሁሉ ለምትኖረው ቤተክርስቲያን የተጻፈ ቢሆንም /17፡20-21/ በመጀመሪያ መፅሐፍ የተፃፈላቸው /original audience/ በኤፌሶንና አካባቢዋ ለሚኖሩ ሰዎች ነው፡፡ እነኚህ ሰዎች አብዛኛዎቹ ጌታን ያመኑና አህዛብ /Gentiles/ የነበሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ይህም ሐዋርያው ዮሐንስ በአንዳንድ ቦታ የአይሁድ ባህልን /custom / እና ሁኔታዎችን ምን ይመስል እንደነበር ሲገልጽ እናያለን፡፡ /2፡6፣ 4፡9፣ 7፡2፣ 10፡22፣ 18፡28 ፣ 19፡31፣ 19፡41፣ 19፡42/ በተጨማሪም መፅሐፍ በቀድሞ ፍልስጤም /Palestine/ የነበሩ ቦታዎችንም መግለጹንም እናያለን፡፡ / 4፡5፣ 5፡2፣ 6፡1፣ 11፡1፣ 11፡18፣ 12፡1፣ 12፡21/

  ስለዚህ የዮሐንስ ወንጌልን በሚገባ ስናጠናና የመፅሐፉን አላማ ስንመለከት መጽሐፉ የተጻፈው <u>በክርስቶስ</u> <u>ላላመኑና የዘላለም ህይወት ላልተቀበሉ ሰዎች</u>፣ <u>በእምነታቸው እየደከሙ ላሉ ክርስቲያኖች</u> ፣ <u>ለአገልጋዮችና</u> <u>በአጠቃላይ በክርስቶስ ለማያምኑ አማኞች በሙሉ ነው፡፡</u> ስለዚህ የዮሐንስ ወንጌል ላልዳኑት ሰዎች የወንጌል መልእክት /evangelistic intent/ ሲኖረው በጌታ ላመኑና ለዳኑ ሰዎች ደግሞ የማስተማር መልእክት /didactic aim/ አለው፡፡

## 1.6 የመፅሐፉ ዋና ዋና አሳቦች ምንድናቸው?

የዮሐንስ ወንጌል የሚያስተምራቸው ዋና ዋና አሳቦች /major themes/ የሚከተሉት ናቸው፡-

- ስለ ጌታ ኢየሱስ ማንነት
- ጌታ ኢየሱስ ወደ ምድር ስለመጣበት አላማ
- ጌታ ኢየሱስ ‹እኔ ነኝ› ያለባቸው
- ሰባት የተመረጡ ተአምራቶች
- ሰባት የተመረጡ ሰፊ ንግግሮች /discourses/
- ስለደህንነትና የዘላለም ህይወት
- ስለመንፈስ ቅዱስ
- ስለእምነት
- ስለጌታ መስቀል
- ስለመጨረሻው ዘመን /Eschatology/
- ስለአለም
- ስለሰይጣን

- ስለጌታ ኢየሱስ መክበር /the glorification of Jesus/
- ስለሰአት /ጊዜ/
- የሚነጻጸሩ ቃላት
- ሁለት ትርጉም ያላቸው ቃላትና የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

## ስለጌታ ኢየሱስ ማንነት /Christology/

- የመጽሐፉ ዋና መልእክት ኢየሱስ ማን እንደሆነ ለማስተማር ነው፡፡ ምክንያቱም የዘላለም ህይወት የሚገኘው የጌታ ኢየሱስን ማንነት በሚገባ በመረዳትና ከእርሱ ጋር አስፈላጊውን ግንኙነት በማድረግ ስለሆነ ነው፡፡
- ጌታ ኢየሱስ ቃል /Logos/ ተብሎ ተጠቅሷል፡፡ ይህም አባባል በዮሐንስ ወንጌል እና በዮሐንስ መልእክት ብቻ የሚገኝ ነው /ዮሐ 1፡2፣ 2ኛ ዮሐ 1፡1፣ ራዕ 19፡13/
- ጌታ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ /መሲሁ/ መሆኑን በተደጋጋሚ ተጽፎአል፡፡ ከሁለት ቦታዎች በስተቀር /1፡17፣ 17፡3/ ክርስቶስ የሚለው የተጠቀሰው እንደ ተውላጠ ስም /proper name/ ሳይሆን እንደ ገላጭ ስም /Title/ ሆኖ ነው፡፡ ስለዚህ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ መሆኑን ማሳወቅ የመጽሐፉ ዋና ሃሳብ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከአራቱም ወንጌላት ውስጥ መሲሁ የሚለውን ቃል የተጠቀሰው ዮሐንስ ወንጌል ላይ ብቻ ነው፡፡ መሲሁ /1፡42፣ 4፡25/ ፣ ክርስቶስ / 1፡20፣ 3፡28፣ 1፡41፣ 7፡52፣ 7፡25-31፣ 7፡40-43፣ 12፡34፣ 4፡29-30/
- ልክ እንደ ሌሎቹ ሶስቱ ወንጌላት ጌታችን ራሱን "የሰው ልጅ" ብሎ የጠራበት መጠሪያ /title/በዮሐንስ ወንጌል በብዛት ተጠቅሷል፡፡ /1፡51፣ 2፡12፣ 3፡13-14፣ 4፡6-7 4፡6-7፣ 5፡27፣ 6፡27፣ 6፡53፣ 6፡62፣ 7፡3-8፣ 8፡28፣ 8፡40፣ 9፡35፣ 11፡33፣ 11፡3፣ 12፡23፣ 12፡27፣ 12፡34፣ 13፡31፣ 19፡25-26፣ 19፡28/ ስለዚህ የዮሐንስ ወንጌል ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው እንደሆነ /በተደጋጋሚ በመግለጽ/ የሚያስተምር መጽሐፍ ነው፡፡ ጌታ ኢየሱስ

ፍጹም ሰው ቢሆንም ምንም ሐጢአት የሌለበት መሆኑን ያስተምረናል /8፡31-59፣ 10፡30፣ 17፡22/

- ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሰው ብቻ ሳይሆን ፍጹም አምላክ መሆኑን በግልጽ በማያሻማ ቋንቋ ከየትኛውም የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በላይ ያስተማረ መጽሐፍ ነው፡፡ ይህንንም ጌታ እራሱ ከአብ ጋር አንድ መሆኑን በመግለጽና እንዲሁም "እኔ ነኝ" /ego eimi/ በሚላቸው አባባሎቹ ፍጹም አምላክ መሆኑን አስተምሯል፡፡ ጌታ ኢየሱስ እራሱን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል መሆኑን በማስተማሩ /5፡28/ እንዲሁም አምላክ መሆኑን በግልጽ በመናገሩ /10፡33/ ትልቅ ተቃውሞ እንደደረሰበት መጽሐፍ በግልጽ ከማስተማሩም በላይ ጌታ ኢየሱስ ይህንን ተቃውሞ ሲቀበል እና አምላክ መሆኑን ሲያረጋግጥ እናያለን፡፡ ስለዚህ የዮሐንስ ወንጌል ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ መሆኑንና የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በግልጽ በማያሻማ ቋንቋ በአዲስ ኪዳን ካሉ መጻህፍት ሁሉ በተለየ መንገድ የተገለጸበት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

- የዮሐንስ ወንጌል ከ100 ጊዜ በላይ ጌታ ኢየሱስ እግዚአብሔር አባቱ መሆኑን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የገለጸበት መጽሐፍ ነው፡፡ ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን ማስተማር አንዱና ዋናው የመጽሐፉ መልእክት ነው /20፡31/፡፡ ሐዋርያው ዮሐንስ የኢየሱስ ክርስቶስ ልጅነትና እኛ ከሚኖረን ልጅነት የተለየ መሆኑን ያስተምራል፡፡ ይህንንም ልዩነት ያሳየው የኢየሱስን ልጅነት ሲገልጽ የተጠቀመው የግሪኩን ቃል /Hyios/ 3-3፡16፣ 3፡18/ እና የኛን ልጅነት ሲገልጽ የተጠቀመው የግሪኩ ቃል / keknathem፡- 1፡12፣ 11፡52/ የተለያየ በመሆኑ ነው፡፡ ይህንንም በማሳየት ጌታ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር የተለየ ግንኙነት እንዳለው ያስተምራል፡፡ ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ ብቸኛውና የተለየው የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን እንማራለን፡፡

- በተጨማሪም ጌታ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ጋር ወደ አለም የተላከ የእግዚአብሔር ልጅ መሆኑን በማስረገጥ ያስተምረናል /3፡17፣ 3፡34፣ 5፡36-38፣ 6፡28.57 ፣ 7፡29፣ 8፡42፣ 10፣36፣ 11፡42፣ 17፡3, 8, 18, 21, 23,25 , ፣ 20፡21/

- ወደአባቱ እንደሚመለስም ተናግሮአል / 13፡1 ፣ 14፡17፣ 14፡12፣ 14፡28፣ 16፡10፣ 20፡17/

- በአባቱ የሚደገፍ መሆኑም ተገልጿል /5፡19፣ 5፡30፣ 14፡31፣ 15፡10/

- አባቱን የሚገልጸው ጌታ ኢየሱስ መሆኑም ተገልጿል /1፡18፣ 6፡46፣ 8፡19፣ 14፡8-9፣ 14፡6፣ 15፡15፣ 12፡49፣ 14፡24/

- አባቱ እንደሚወደው ተገልጻል /The object of the father's Love/ /3፡35፣ 5፡20፣ 10፡17፣ 17፡24፣ 13፡34-35/

- በዮሐንስ ወንጌል ‹የእግዚአብሔር ልጅ› የሚለው ቃል በሰፊው ተጠቅሷል፡፡ ከሌሎች ወንጌላት ጋር ለማወዳደር ቃሉ በማርቆስ 4 ጊዜ ፣ በሉቃስ 6 ጊዜ፣ በማቴዎስ ወንጌል 23 ጊዜ ሲጠቀስ በዮሐንስ ወንጌል ግን 107 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ ይህም ሐዋርያው የጌታን ማንነት ለማሳየት የተጠቀመበት አስፈላጊ ነገር ነው፡፡

<u>ሰባቱ ተአምራቶችና ሰባቱ ሰፊ ንግግሮች</u>

- በዮሐንስ ወንጌል ላይ <u>የተመረጡ ሰባት ተአምራቶችና</u> /ትንሳኤውን ሳይጨምር/ <u>ሰባቱ ሰፋ ያሉ የኢየሱስ ትምህርቶችና ንግግሮች</u> /discourses/ እናገኛለን፡፡

<u>ሰባቱ ተአምራቶች</u>

1. ውሃውን ወደ ወይም ጠጅ የለወጠበት /ዮሐ 2፡1-11/
2. የተፈወሰው የሹሙ ልጅ /ዮሐ 4፡46-54/
3. ከ38 አመት ጀምሮ የታመመው ሰው የተፈወሰበት /ዮሐ 5፡1-9/
4. 5000 ሰዎችን በአምስት እንጀራና በሁለት አሳ መመገቡ /ዮሐ 6፡1-14/
5. ጌታ በባህር ላይ እየሄደ መምጣቱ /ዮሐ 6፡16-21/
6. ከመወለዱ ጀምሮ እውር የነበረውን ሰው መፈወሱ /ዮሐ 9፡1-41/
7. አልአዛርን ከሞት ማስነሳቱ /ዮሐ 11፡1-44/

<u>ሰባቱ የጌታ  ኢየሱስ ሰፊ ንግግሮችና ትምህርቶች /discourses/</u>

1. ከኒቆዲሞስ ጋር የተነጋገረበት /3፡1-21/
2. ከሳምራዊቷ ሴት ጋር የተነጋገረበት /4፡4-26/
3. ከአይሁድ መሪዎች ጋር የተነጋገረበት /5፡16-47/
4. በቅፍርናሆም ካሉ ህዝቦች ጋር የተነጋገረበት / 6፡25-59/ /The bread of life discourse/
5. እንደገና ከአይሁድ መሪዎች ጋር የተነጋገረበት /8፡12-59/ /light of the world discourse/
6. ከፈሪሳውያን ጋር የተነጋገረበት /10፡1-21 / /Good shepherd discourse/
7. ከደቀመዛሙርቱ ጋር ሲሰናበት የተነጋገረበት /13፡31-17፡26/ /Farewell discourse to his disciples/

- በእያንዳንዱ ተአምራት ላይ ጌታ ተአምራት የሰራው እንዲሁ ለመስራት ብቻ ሳይሆን በአላማ ነው፡፡ /ለምሳሌ እውሩን ሲያበራ እርሱ የአለም ብርሃን መሆኑን ለማሳየት ፣ የተራቡትን ሲመግብ ደግሞ የህይወት እንጀራና ምንጭ መሆኑን ለማስተማር ነው፡፡/ በዚህ መሰረት ተአምራት የመስራቱ ዋና አላማም ኢየሱስ ማን መሆኑን ለመግለጽ ነው፡፡ ስለዚህ እያንዳንዱን ተአምራት የሚያጠና ሰው ‹ኢየሱስ ማን ነው?› የሚል ጥያቄ የሚፈጥርና ምንነቱንም በግልጽ የሚያስተምር ነው፡፡ ከላይ የተገለጹትና ከምዕራፍ 2፡11 እስከ 11፡44 ድረስ ያሉት 7ቱም ተአምራቶች ጌታ ኢየሱስ ከሰማይ የመጣ መሆኑን / divine origion /፣ መለኮታዊ ስልጣን /divine authority/ ያለው መሆኑን፣ እንዲሁም ሙሉ በሙሉ አምላክ መሆኑን ያስተምራሉ፡፡ ይህንንም ሐዋርያው እራሱ በግልጽ ጠቅሶታል፡፡ /10፡37-38/፡፡
- እያንዳንዱ ንግግሮችና ትምህርቶችም /discourses/ ዋና አላማቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ማን እንደሆነ መግለጽና ማስተማር ነው፡፡
- <u>ጌታ ‹እኔ ነኝ› ያለባቸው /with predicate/</u>

1. የህይወት እንጀራ እኔ ነኝ /6፡35/

2. የአለም ብርሃን እኔ ነኝ /8፡12፣ 9፡5/

3. እኔ የበጎች በር ነኝ /10፡7/

4. መልካም እረኛ እኔ ነኝ /10፡11፣ 10፡14/

5. ትንሳኤ እና ህይወት እኔ ነኝ /11፡25/

6. እኔ መንገድና እውነት ህይወት ነኝ /14፡6/

7. እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ /15፡1/

- ጌታ ‹እኔ ነኝ› /ego eimi/ ያለባቸው /absolute/
    - ዮሐ 8፡58 <Before Abraham was I am>
    - ይህ ጌታ ኢየሱስ ‹እኔ ነኝ› እያለ ያስተማራቸው ትምህርቶች ፍጹም አምላክ መሆኑን የሚያመለክቱና በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ራሱን ከገለጸባቸው ሃሳቦች ጋር የሚገናኙ ናቸው /ዘፀ 3፡14 ፣ ኢሳ 41፡4 ፣ ኢሳ 43፡10፣ ኢሳ 46፡4/

- ጌታ ኢየሱስ ‹የእግዚአብሔር በግ›
    - ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ‹የእግዚአብሔር በግ› ተብሎ ተጠርቶአል /1፡29፣ 1፡36/ ይህም መጠሪያ ስም /title/ ስለጌታ ኢየሱስ ተልእኮ የሚያስተምር ሲሆን የህዝቡን ሐጢአት በማስወገድ የመረጣቸውን ህዝቦቹን መዋጀት ነው፡፡ ይህም ከብሉይ ኪዳን አሳብ ጋር ይገናኛል /ኢሳ 53፡7፣ ዘፀ 12፡22/

ጌታ ወደምድር የመጣበት አላማ፣

- ሌላው ዋናው የመጽሐፉ ሃሳብ ጌታ ኢየሱስ ወደምድር የመጣበትን አላማ በግልጽ ማስተማር ነው። ይህም አላማው በመስቀል ላይ በመሞት /2፡4፣ 12፡23፣ 12፡27፣ 13፡1፣ 17፡1፣ 10፡11፣ 10፡17/ ለሰው ልጆች ህይወት መስጠት መሆኑን በተደጋጋሚ እና በጥልቀት ተገልጿል / 5፡21፣ 3፡35፣ 6፡40፣ 6፡47፣ 10፡10፣ 11፡25፣ 17፡2/

- በአጠቃላይ የዮሐንስ ወንጌል ዋናው መልእክት /Theme/ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሌሎቹ የተጠቀሱት መልእክቶች በሙሉ ማለትም ስለደህንነት፣ ስለመጨረሻው ዘመን፣ ስለቤተክርስቲያን፣ ስለአለም በሙሉ የዋናው መልእክት ክፍል ከመሆናቸውም በላይ በክርስቶስ ማንነት ዙሪያ የሚታዩ ናቸው።

- የመጽሐፉ መልእክት ዋናው ሃሳብ የሆነው ጌታ ኢየሱስ ከዚህ በታች በተዘረዘሩትና በጣም አስደናቂ በሆነ መንገድ ተገልጾ እናገኛለን።

1. ቃል /1፡1 ፣ 1፡14/
2. የእግዚአብሔር ልጅ /1፡34/
3. ልጁ /3፡17፣ 3፡36፣ 5፡19-27/
4. የሰው ልጅ /1፡51/
5. ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጣ መምህር /3፡2/
6. ነብይ /4፡19፣ 9፡19/
7. ወደአለም የሚመጣው ነብይ /6፡14/
8. መሲሁ /1፡41፣ 4፡29፣ 11፡11 ፣ 11፡20፣ 11፡30/
9. የእስራኤል ንጉስ /1፡49/
10. የአይሁድ ንጉስ /19፡19/
11. የህያው እግዚአብሔር ልጅ /The Holy one of God/ /6፡69/
12. የእግዚአብሔር በግ /1፡29፣ 1፡36/

13. የሚመጣው /12፡13/

14. ሰውየው /the man/ /19፡5/

15. በእግዚአብሔር የተላከው /3፡16 -17፣ 3፡34፣ 5፡30፣ 7፡16-18፣ 10፡36/

16. እኔ ነኝ /8፡58/

17. ረቡኒ /20፡16/

18. ጌታ /20፡18፣ 27፡7/

19. ጌታዬና አምላኬ /20፡28/

20. ወዘተ

## ደህንነት

እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያቀደውና ያዘጋጀው የደህንነት መንገድ ምን እንደሆነ ማስተማር አንዱና ዋናው የዮሐንስ ወንጌል መፅሐፍ አሳብ /theme/ ነው፡፡ መፅሐፉ በተደጋጋሚ ሰዎች ‹ኢየሱስ ማን ነው?› የሚለውን ጥያቄ እንዲያነሱ የሚጋብዝ ሲሆን በምላሹም ኢየሱስ ሰዎችን ለማዳን ከአባቱ ዘንድ ተልኮ የመጣ መሆኑን ያስተምራል /3፡16-17/

## አዲስ ልደት /እንደገና መወለድ/

ስለአዲስ ልደት የሚያስተምረው ክፍል የሚገኘው በ3፡1-21 ባለው ክፍል ውስጥ ነው ዳግመኛ መወለድ የሚለው የግሪኩ ቃል /anothen/ ትርጉሙ እንደገና /again/ ወይም ከላይ /above/ የሚለውን ሃሳብ ያስተምረናል፡፡ ስለዚህ ሰው የእግዚአብሔርን መንግስት ለመውረስ እንደገና መወለድ እንዳለበት ወይም ከላይ መወለድ እንዳለበት የሚያስተምር እጅግ አስፈላጊ የሆነ ክፍል ነው፡፡ ይህም ዳግመኛ መወለድ በፍጹም የሰዎች ስራ አለመሆኑንና /3፡6/ ሙሉ በሙሉ የመንፈስ ቅዱስ ስራ መሆኑን /3፡8/ ክፍሉ በግልጽ ያስተምረናል፡፡

## <u>የጌታ መሰቀል</u>

የዮሐንስ ወንጌል መጽሐፍ የጌታን መሰቀል ወደምድር ከመጣበት ተልእኮ ዋናው መሆኑን ከማሳየት ባሻገር ወደመጣበት ወደአባቱ አላማውን ፈጽሞ የሚመለስበት መሆኑንም ያሳያል /17፡4፣ 19፡28/

የጌታ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ መሞት እግዚአብሔር አለምን ለማዳን ያዘጋጀው ዋናው መንገድ /central/ ስለሆነ በዚህ መጽሐፍ ላይ የጌታ መያዝ /arrest/ ፣ መከሰስ /trial/ እና መሰቀል የተደረገው <u>በድንገተኛ ሁኔታ</u> ሳይሆን <u>በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሃሳብ</u> መሆኑን በሚገባ ያስተምራል /2፡4 ፣ 7፡6፣ 7፡8፣ 7፡30፣ 8፡20፣ 12፡23፣ 12፡24፣ 12፡27/፡፡

የጌታ ወደምድር የመጣበት ተልእኮ መስቀሉን የሚያካትት ስለሆነ ገና ከአገልግሎቱ መጀመሪያ ስለመስቀሉ መሰረት የሚጥል ትምህርት ያስተምራል /3፡17/፡፡

በአጠቃላይ ጌታ የተያዘው፣ የተከሰሰውና የተሰቀለው በአጋጣሚ ወይም ሳያስበው ወይም ሳይፈልገው ወይም በድንገት ሳይሆን <u>ዘላለማዊ በሆነ በእግዚአብሔር አሳብ መሆኑን በግልጽ ያስተምረናል፡፡</u> /13፡1፣ 13፡21-27፣ 13፡36፣ 14፡2፣ 14፡12፣ 14፡19፣ 14፡28፣ 16፡5፣ 16፡16፣ 16፡28፣ 17፡1፣ 17፡4፣ 17፡11፣ 17፡13/

ጌታ የሚሞተው በፍጹም በራሱ ፈቃደኝነት መሆኑን በሚገባ መፅሐፉ ያስተምረናል /10፡1-22፣ 15፡13/

ጌታ ወደመስቀሉ ሲሄድ ሂደቱን የሚቆጣጠረው የካደው ይሁዳ ሳይሆን፣ ሊቀካህኑ ሳይሆን ወይም ጲላጦስ ሳይሆን ራሱ ጌታ መሆኑን ያስተምረናል /18፡6፣ 18፡8፣ 19፡11፣ 19፡26፣ 19፡27፣ 19፡28፣ 19፡30/

ጌታ የሞተው ሞት የመስዋእትነት ሞት መሆኑንም ያስተምረናል /1፡29፣ 1፡36፣ 6፡51/

## <u>እምነት</u>

መጽሐፉ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚያውቁት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በሚኖራቸው እምነት ብቻ መሆኑን ያስተምራል /1፡12፣ 20፡31፣ 9፡1-41፣ 6፡61/

አጠቃላይ የመጽሐፉ አላማ በ20፡31 ላይ እንደተጠቀሰው ሰዎች በጌታ አምነው የዘላለም ህይወት እንዲያገኙ ስለሆነ ይህ አሳብ ማለትም በጌታ ማመን በመጽሐፉ በዝርዝር በስፋት ተጽፎ እናገኛለን፡፡

ሰዎች በጌታ በሚያምኑበት ወቅት፣ ማለትም ኢየሱስ ማን መሆኑን ፣ የመጣበትን አላማ፣ የሰራውን ስራ፣ በተለይ ደግሞ ለሰዎች ደህንነት ሲል የከፈለውን ዋጋ <u>ሲያምኑና ሲቀበሉ</u> ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ግንኙነት ይጀምራሉ /1፡12/

በመፅሐፉ ጌታ ኢየሱስን ማመንና ወደ እርሱ መምጣት አንድ እንደሆነ ተጠቅሷል /6፡35፣ 7፡37-38፣ 6፡28/

እምነት /faith , believe / የሚለው ቃል በሌሎቹ ሶስቱ ወንጌላት በግልጽ ያልተፃፈ ነገር ግን በዮሐንስ ወንጌል በግልጽ የተጻፈ አሳብ ነው፡፡

## የዘላለም ህይወት

መጽሐፉ እንደሚያስተምረን የዘላለም ህይወት ማለት በሚመጣው ዘመን የምናገኘው ነገር ብቻ ሳይሆን አሁን በምንኖረው ኑሮ ልንለማመደውና በአሁኑ ኑሮአችንም የተሰጠ መሆኑን ያስተምረናል፡፡ /6፡40፣ 6፡54፣ 6፡39፣ 6፡44፣ 11፡24፣ 12፡48፣ 5፡29/

የዘላለም ህይወት በክርስቶስ ማግኘት ዋናውና ቁልፍ የሆነው የዮሐንስ ወንጌል መልእክቱ ነው፡፡

## የጌታ መክበር /The glorification of Jesus/

በዮሐንስ ወንጌል የጌታ መክበር የተገለጸው በሞቱ፣ በትንሳኤው፣ በማረጉና ከፍ ከፍ በማለቱ ነው /7፡39፣ 12፡16/፡፡ የጌታ መክበር የጀመረው ሲወለድ ወይም አገልግሎቱን ሲጀምር ወይም ተአምራቶቹን ሲያደርግ አይደለም፡፡ ነገር ግን ጌታ አለም ሳይፈጠር በፊት የከበረ መሆኑን መጽሐፉ ያስተምረናል /17፡5፣ 12፡41/

በዚህ መጽሐፍ የጌታ ኢየሱስ ወደታች መውረድና ወደሰማይ መውጣት በሚገባ ተገልጿል፡፡ የዚህም ገለጻ ዋናው አላማ ጌታ ኢየሱስ የነበረ /preexistence/ መሆኑንና የከበረ /exalted/ መሆኑን ለማስተማር ነው፡፡

## መንፈስ ቅዱስ

በዮሐንስ ወንጌል በብዙ ስፍራ /በተለይ ከምዕራፍ 14-17/ ስለመንፈስ ቅዱስ ምንነትና ስራ ለክርስትና ህይወታችን የሚጠቅሙ ብዙ ጠቃሚ አሳቦች ተገልጸዋል፡፡ መጽሐፉ ስለጌታ መንፈስ ቅዱስ ከሌሎቹ ወንጌላት በተለየ መንገድ ያስተማረ መፅሐፍ ነው፡፡

ስለመጥምቁ ዮሐንስ በሚናገረው ክፍል ውስጥ ሁለት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በጌታ ላይ እንደሚመጣና በእርሱ ላይ እንደሚኖር ተጠቅሷል /1፡32 ‹መንፈስ ቅዱስ . . . በዕርሱ ላይም ኖረ፡፡›፣ 1፡33 ‹መንፈስ ሲወርድበትና ሲኖርበት የምታየው . . . › ይህም አሳብ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስና በጌታ ኢየሱስ መካከል ያለው ግንኙነት ቋሚ

/permanent/ መሆኑን ስለሚያመለክት ነው። በ1፡32-33 ባለው ክፍል የተጠቀሰውና በእርሱ ላይ ይኖራል የሚለው የግሪኩ ቃል / emeinen ep auton/ ውስጣዊ የሆነና ዘለቄታዊ የሆነ በጌታና በመንፈስ ቅዱስ መካከል የሚኖር ግንኙነትን የሚያስተምር ክፍል ነው ። /an, inward, enduring personal communion/. ይህም ቃል በምዕራፍ 14፡10-11 ባለው ክፍል ውስጥ በአብና በወልድ መካከል የሚኖረውን የጋራ የሆነ የጠበቀና ዘላቂታዊ ግንኙነትን / permanent mutual indwelling relationship/ ለማሳየት ተጠቅሷል።

ይህ በአብና በወልድ መካከል ያለው ግንኙነት በእግዚአብሔርና በአማኞች መካከል ያለውን ግንኙነት ያስተምራል /1ዮሐ 4፡15/ አማኞችም ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ይገልጻል /15፡5-6/። በተጨማሪ ከጌታ ቃል ጋር ያለውን ግንኙነትም ያሳያል /8፡31/።

ይህ ቃል በጣም ጠቃሚ ነው ምክንያቱም ይህ የእውነት መንፈስ መጥቶ በአማኞች ላይ በማረፍ በቋሚነት /permanently / አብሮ እንደሚሆን በግልጽ ስለሚያስተምር ነው። /14፡17፣ 16፡7/

ዳግመኛ መወለድ / regeneration/ የሚቻለው በሰዎች ጥረት ወይም ድካም ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ስራ ብቻ መሆኑን መፅሐፉ ያስተምረናል። /3፡5/ በአጠቃላይ አማኞች መንፈሳዊ ኑሮ መኖር የሚችሉት በመንፈስ ቅዱስ ሐይልና እርዳታ ብቻ መሆኑንም ያስተምረናል። /The entire spiritual existence of a believer depends on the work of the Holy Spirit/ /6፡63፣ 7፡38-39/

- በምዕራፍ 14-17 ላይ የተጠቀሰው ጰራቅሊጦስ / <Paraclete> / የሚለው የግሪክ ቃል መንፈስ ቅዱስ አፅናኝ /Comforter / ብለን ከምንጠራው የበለጠ ትርጉምና ሐሳብ የያዘ ነው። ይህ መንፈስ ቅዱስ በአንድ የፍርድ ቦታ ከጎን ቆሞ የሚረዳ፣ የሚማልድ፣ የሚሟገት /pleader/ ወይም ስለአማኞች የሚከራከር / Character witness defender/ እንደሆነ የሚያስተምር ጥልቀት ያለው ቃል ነው። ይህም መንፈስ ቅዱስ ምን ያህል ታላቅ የሆነ ቦታ በክርስትና ህይወታችን እንዳለው የሚያስረዳ ክፍል ነው።

## ሰአት

ሰአት የሚለው ሃሳብ ከጌታ ኢየሱስ ከፍ ከፍ ማለት ጋር በተያያዘ መንገድ ብዙ ነገሮችን ያስተምረናል ። / 2፡4፣ 4፡21፣ 4፡23፣ 5፡25፣ 5፡28፣ 7፡30፣ 8፡20፣ 12፡23፣ 12፡27፣ 13፡1፣ 16፡21፣ 17፡1/

## የመጨረሻው ዘመን /Eschatology/

ለዮሐንስ ወንጌል የመጨረሻው ዘመን በአብዛኛው ወደላይ Vertical dimension ሲኖረው ወደጎን Horizontal dimension አለው፡፡ /3፡13፣ 6፡62፣ 8፡34፣ 3፡17፣ 3፡34፣ 5፡36-38፣ 6፡29፣ 6፡57፣ 7፡29፣ 8፡42፣ 10፡36፣ 11፡42፣ 17፡3፣ 17፡8፣ 17፡18፣ 17፡21፣ 17፡23፣ 17፡25፣ 20፡21፣ 13፡1፣ 14፡12፣ 14፡28፣ 16፡10፣ 16፡28፣ 20፡17/

/20፡21፣ 12፡25፣ 21፡22፣ 6፡39፣ 6፡44፣ 6፡51፣ 5፡25፣ 5፡28-29፣ 12፡48፣ 3፡18-19/

## የሚነጻጸሩ አሳቦች /Polarization/

በዮሐንስ ወንጌል የሚነጻጸሩ ሁለት ነገሮችን እናገኛለን

- ብርሐንና ጨለማ /1፡4-9/
- ፍቅርና ጥላቻ /15፡17-18/
- ከላይና ከታች /8፡23/
- ህይወትና ሞት /6፡57-58/
- እውነትና ውሸት /8፡32-47/
- መንፈስና ስጋ /1፡13፣ 1፡14፣ 3፡6፣ 3፡12፣ 6፡63/
- ሰማይና ምድር /3፡12፣ 8፡23/
- ማመንና አለማመን /3;18/

እነኚህን ነገሮች ደጋግሞ በማሳየት መጽሐፉ ሰዎች ሁለት የተለያየ ምርጫ /alternative choice/ እንዳላቸው ያስተምራል፡፡ ይህም ለጌታ ኢየሱስ ጥሪ ምላሽ ከመስጠት አኳያ የሰዎች ምርጫ በጣም ወሳኝ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ምክንያቱም መጨረሻቸው የሚወሰነው ለጌታ በሚሰጡት ምላሽ ስለሆነ ነው፡፡ በተጨማሪ መሀከለኛ የሆነ መንገድ እንደሌለ በግልጽ የሚያስተምር እጅግ ጠቃሚ አሳብ ነው፡፡

## ሁለት ትርጉም ያላቸው ቃላት /word plays/

መፅሐፉ ሁለት ትርጉም ያላቸው ቃላት በመጠቀም ይታወቃል፡፡

| | |
|---|---|
| 1:5 - The light comprehended | Overcome |
| | understand |
| 3:3 - ዳግመኛ መወለድ | እንደገና /again/ |
| | ከላይ /above/ |
| 4:11 – Living Water | Flowing |
| | Living |
| 7:8 – go up | Go up to Jerusalem |
| | Return to the Father |

## 1.6 የዮሐንስ ወንጌል ከሌሎቹ ሶስት ወንጌላት /synoptic Gospels/ የሚለየው በምንድነው?

1. በሶስቱ ወንጌላት /synoptics/ የጌታ ኢየሱስ አገልግሎት /ከመጨረሻው ሳምንት በስተቀር/ በአብዛኛው የሚያተኩረው በገሊላ ብቻ ነው። ነገር ግን በዮሐንስ ወንጌል የጌታ አገልግሎት የሚያተኩረው ብዙው በኢየሩሳሌም በሚያደርገው ነው።
2. የጊዜው ልዩነት አለ። በሶስቱ ወንጌላት አንድ የፋሲካ በአል ብቻ ስለተጠቀሰ የአንድ ወይም የሁለት አመት ወቅት /event/ ብቻ እናገኛለን። ነገር ግን የዮሐንስ ወንጌል ቢያንስ ሶስት ፋሲካ ተጠቅሷል /2:13፣ 6:4፣ 13:1/ ምናልባት አራት ሊሆን ይችላል /5:1/።
3. በዮሐንስ ወንጌል ያልተጠቀሱ ነገር ግን በሶስቱ ወንጌላት የተጠቀሱ ብዙ ነገሮች አሉ።

**ለምሳሌ**

- የጌታ መወለድና የልጅነት ታሪኩ
- የጌታ መጠመቅ

- በተራራው ላይ መለወጡ /transfiguration/
- አጋንንት የማውጣት ሂደት
- በጌተሰማኒ ስቃይ መቀበሉ
- የጌታ እራት ሂደት /institution of the lord's supper/
- የጌታ የትውልድ ሃረግ
- የመጥምቁ ዮሐንስ ስብከት
- የጌታ በምድረበዳ መፈተን
- የተራራው ስብከት
- የመጥምቁ ዮሐንስ ጌታን መጠራጠር
- ምሳሌዎች
- አስራሁለቱን ወይም ሰባውን ለአገልግሎት መላኩ
- ለምጻሙን መፈወሱ
- አራት ሺ መመገቡ
- የጴጥሮስ ምስክርነት /Peter's Confession/
- ወዘተ

4. በአጻጻፍ ስልታቸውም ይለያያሉ /literary usage/ በሶስት ወንጌላት ግልጽ የሆኑ ፣ አጫጭር የሆኑና በቀላሉ ለማስታወስ የሚቻሉ የኢየሱስ ትምህርቶች ሲኖሩ በዮሐንስ ወንጌል ግን ረጃጅም የሆኑ ትምህርቶችና ንግግሮች /discourses/ ይገኛሉ፡፡

5. በሶስቱ ወንጌላት <u>የእግዚአብሔር መንግስት</u> /The kingdom of God/ የሚለው ሃሳብ የወንጌላቱ ዋና ክፍል ሲሆን በዮሐንስ ወንጌል ግን የተጠቀሰው ሁለት ቦታ ብቻ ነው /3፡3፣ 3፡5፣ 18፡36/፡፡ ነገር ግን በዚህ ፋንታ <u>የዘለአለም ህይወት /Eternal life/</u> የሚለው ሃሳብ በዮሐንስ ወንጌል ላይ ማዕከላዊ /central/ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

6. እንዲሁም በሶስቱ ወንጌላት ያልተጠቀሰና በዮሐንስ ወንጌል ብቻ የተጠቀሱ ነገሮች አሉ፡፡ ከዚህም ውስጥ የመጽሐፉ ዋና መለያ የሆነው ጌታ ‹እኔ ነኝ› እያለ ያስተማረው ትምህርት አንዱ ነው፡፡

7. የዮሐንስ ወንጌል ቅርጽ /structure/ ከሌሎቹ ሶስት ወንጌላት ይለያል፡፡

8. አለም /Kosmos/ የሚለው ቃል በሶስቱ ወንጌላት ላይ ጥቂት ቦታ ብቻ የተጠቀሰ ሲሆን በዮሐንስ ወንጌል ግን ብዙ ሃሳቦችን ለማስተማር በተደጋጋሚ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡

9. በሶስቱ ወንጌላት በብዛት ያልተጠቀሱ ነገር ግን በዮሐንስ ወንጌል ላይ በብዛት የምናገኛቸው ቃላቶች አሉ፡፡ ለምሳሌ መውደድ /to love/፣ ፍቅር /love/፣ እውነት /truth/፣ እውነት /true/፣ እውነት /genuine/ ፣ ማወቅ/to know/፣ መስራት /to work/፣ አለም /world/፣ መፍረድ /to judge /፣ አብሮ መሆን /to abide /፣ መላክ /to send/፣ መመስከር / to witness/፣ በተለይ ደግሞ ማመን /to believe/

እንዲሁም በሶስቱ ወንጌላት ላይ በብዛት የተጠቀሱት በዮሐንስ ወንጌል ላይ ግን በብዛት የማናገኛቸው ቃላቶች አሉ፡፡ ከነኚህም መካከል ፅድቅ /Righteousness/,፣ ሐይል ወይም ተአምር /Power or Miracle/ ፣ መማር ወይም መራራት /To feel mercy or pity/፣ መጥራት /To call/፣ ንስሃ መግባት /To repent/፣ ምሳሌ /Parable/፣ መጸለይ /to pray/ ይገኙበታል፡፡

10. ሌላው ልዩነት በሶስቱ ወንጌላትና በዮሐንስ መካከል ያለው የማነጻጸር ሂደት /dualism/ ነው፡፡ በሶስቱ ወንጌላት ላይ የምናየው ማነጻጸር ሁል ጊዜ ወደጎን /Horizontal/ ነው፡፡ ማለትም የአሁኑን አለምና የሚመጣውን አለም /this age and the age to come/ ነው፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ያለው ማነጻጸር ግን በአብዛኛው ወደላይ /Vertical/ ነው፡፡ ማለትም በላይ ያለው አለምና /the world above/ በታች ያለው አለም /the world below / /8፡23፣ 16፡11፣ 11፡9፣ 18፡36፣ 13፡1፣ 3፡13፣ 6፡38፣ 6፡33፣ 6፡41፣ 6፡50፣ 6፡51፣ 6፡58፣ 6፡62፣ 20፡17/

11. በሶስቱ ወንጌላት ስለሃጢአት የተገለጸው ሃሳብ የሚያመለክተው ሃጢአትን ስለመስራት /act of sin/ነው፡፡ ነገር ግን በዮሐንስ ወንጌል ሃጢአት የበለጠ ትንታኔና ትኩረት /emphasis/ ተሰጥቶት ነው የተገለጸው፡፡ ዮሐንስ ወንጌል ሃጢአት የሚገለጸው በክርስቶስ ባለማመን ነው፡፡ /16፡8፣ 8፡24፣ 1፡5/ /ሃጢአት ጨለማ ነው /፣ 12፡36/

በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ በኢየሱስ አለማመን እግዚአብሔርን መጥላት እንደሆነ ስለተገለጠ /3፡19-21፣ 8፡24/ በክርስቶስ የማመን አስፈላጊነት ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶት እናገኛለን፡፡

12. ኢየሱስ ቃል /Logos /መሆኑን የምናገኘው በዮሐንስ ወንጌል /መልእክቶቹን ጨምሮ/ ብቻ ነው፡፡

13. በሶስቱ ወንጌላት በሚገባ ግልጽ ያልነበረው /explicit/ በዮሐንስ ወንጌል ግን በግልጽ የተጻፈው /explicit/ ጌታ ኢየሱስ ከሰዎች የሚጠብቀውና የዘለአለም ህይወት ማግኘት የሚቻልበት መንገድ ሲሆን ይኸውም እርሱን ማመን /faith, believe/ ነው፡፡

14. የዮሐንስ ወንጌል ከሶስቱ ወንጌላት በበለጠና በስፋት ስለመንፈስ ቅዱስ እና ስለስራው ያስተምራል፡፡

15. በአጠቃላይ ዮሐንስ የተመረጡ 7 ተአምራቶችን 7 ሰፊ ንግግሮችን ትምህርቶችን /discourses/ እንዲሁም ጌታ ‹እኔ ነኝ› ያለባቸውን በስፋት በማሳየት ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ እንደሆነና ከአብ የተላከ እንደሆነ ያስተምራል፡፡

## 1.7 <u>የመጽሐፉ ማውጫ /out line/</u>

<u>የዮሐንስ ወንጌል ማውጫ</u>

I. መግቢያ /1፡1-18/

II. የአገልግሎቱ ጅማሬ /1፡19-51/

   1. የመጥምቁ ዮሐንስ ምስክርነት /1፡19-34/
   2. የመጀመሪያዎቹ ደቀመዛሙርት ምስክርነት /1፡35-52/

III. ከቃና ዘገሊላ እስከ ቃና ዘገሊላ /2፡1-4፡54/

   1. የቃና ዘገሊላው ሰርግ /2፡1-11/
   2. ቤተመቅደሱን ማንጻት /2፡12-25/

3. ወደእግዚአብሔር መንግስት መግባት /3፡1-21/

4. ተጨማሪ የዮሐንስ ምስክርነት /3፡22-36/

5. የሰማሪያይቱ ሴት /4፡1-42/

6. በቃና ዘገሊላ ልጁ የተፈወሰለት ሹም /4፡43-54/

IV. በኢየሩሳሌም በአል ወቅት /5፡1-47/

1. የቤተሳይዳው ፈውስ /5፡1-15/

2. ኢየሱስ ሰንበትና እግዚአብሔር አብ አባት /5፡16-47/

V. በገሊላ በፋሲካ ወቅት /6፡1-71/

1. አምስት ሺ መመገብ /6፡1-15/

2. በውሃው ላይ መሄድ /6፡16-21/

3. ብዙ ህዝብ ማስተማር /6፡22-71/

VI. በኢየሩሳሌም በዳስ በአል ወቅት /7፡1-10፡21/

1. ወደኢየሩሳሌም መውጣት /7፡1-13/

2. አይሁድን ማስተማር /7፡14-8፡59/

3. ፈውስና ትምህርት /9፡1-10፡21/

VII. በኢየሩሳሌም በመቅደስ መታደስ ወቅት /10፡22-42/

VIII. በፋሲካ በአል በኢየሩሳሌም እና በአቅራቢያው /11፡1-12፡50/

1. የሞተውን ማስነሳት /11፡1-44/

2. ጌታ ኢየሱስን የመግደል ሴራ /11፡45-57/

3. በቢታኒያ መቀባት /12፡1-8/

4. የድል መግባት /12፡9-19/

5. የአህዛብ ምላሽ /12፡20-36/

6. የአይሁድ ምላሽ /12፡37-50/

IX. የኢየሱስ አገልግሎት ለደቀመዛሙርት /13፡1-17፡26/

1. የእግር ማጠብና ጌታን መከዳት መነገር /13፡1-38/

2. የመሰናበቻና /farewell/ ትምህርት /14፡1-16፡33/

3. የሊቀካህን ጸሎት /17፡1-26/

X. የአገልግሎት የመጨረሻው ደረጃ /18፡1-20፡31/

1. የኢየሱስ መያዝና መከሰስ /18፡1-19፡16/

2. የኢየሱስ መሰቀል መሞትና መቀበር / 19፡17-42/

3. የኢየሱስ ከሞት መነሳትና መታየት /20፡1-31/

XI. ማጠቃለያ / Epilogue/ /21፡1-25/

1. ተአምራት በባህር ዳር /21፡1-14/

2. የጴጥሮስ አገልግሎት ማረጋገጫ /21፡15-19/

3. ጌታ የሚወደው ደቀመዝሙር /21፡20-23

4. የማጠቃለያ ሃሳብ /21፡24-25/

## 2. የዮሐንስ ወንጌል ለምን እናጠናለን ? ወይም የዚህ ጥናት አላማ ምንድነው?

- የእግዚአብሔር ቃል ስለሆነ /2ኛ ጢሞ 3፡16/
- እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያዘጋጀውን ብቸኛውን የደህንነት መንገድ ኢየሱስ ክርስቶስን ማመንና መቀበል መሆኑን በሚገባ ለመማር
- ስለዳግመኛ መወለድ ምንነትና አስፈላጊነት ለመማር
- የጌታ ኢየሱስን ማንነት በሚገባ ለመማር
- ጌታ ኢየሱስ ወደምድር የመጣበትን ዋና አላማ ለመማር
- የሐጢአትን ምንነትና ትልቅነት ለመማር
- ስለዘላለም ህይወት ለመማር

- ስለመንፈስ ቅዱስና በአማኞች ህይወት ውስጥ ስለሚሰራው ስራ ለመማር
- ወደእግዚአብሔር መንግስት ለመግባት ስለእምነት አስፈላጊነት ለመማር
- ስለመጨረሻው ዘመን ለመማር
- ስለአለምና ስለሰይጣን ለመማር

## 3. ጥናቱ የተዘጋጀው ለማን ነው?

ሀ. በቤተክርስቲያን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ለሚያደርጉ ህብረቶች

ለ. በቤተሰብ ለሚደረጉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች

ሐ. በማንኛውም ህብረቶች ለሚደረጉ የመፅሐፍ ቅዱስ ጥናቶች

መ. እንዲሁም የዮሐንስ ወንጌል ለማስተማር ለሚፈልጉ አገልጋዮች

## 4. የአጠናን ዘዴ

ሀ. የዮሐንስ ወንጌልን መጽሐፍ ደጋግሞ ማንበብ

ለ. ለመግቢያ የተዘጋጀውን ፅሑፍ በሚገባ ማጥናት

ሐ. የቃሉ ባለቤት መንፈስ ቅዱስ ቃሉን እንዲያበራልን አጥብቆ መጸለይ

መ. ከጥናቱ በፊት ለዕለቱ የተዘጋጁትን ጥያቄዎች በሚገባ ሰርቶና ተዘጋጅቶ መምጣጥ

## 5. ጥናቱ በግምት የሚፈጀው ጊዜ

በየሳምንቱ የሚጠና ከሆነ ከ4 – 6 ወር ይፈጃል፡፡ ይህም ጥናቱን አብረው በሚያጠኑ ሰዎች ቁጥር ላይ የተመረከዘ ይሆናል፡፡

## 6. የዮሐንስ ወንጌልን ለማጥናት የሚረዱ ጥያቄዎች

## ሀ. የመፅሐፍ መግቢያ /Prologue/ /1፡1-51/

1. ጌታ ኢየሱስ ቃል ተብሎ የተገለጠው በዮሐንስ ወንጌል 1፡1-18፣ በአንደኛ ዮሐንስ መልእክት 1፡1 እና በዮሐንስ ራዕይ 19፡13 ብቻ ነው፡፡ በዮሐንስ ወንጌል ጌታ ኢየሱስ ቃል ተብሎ ሲጠቀስ ምን ማለት ይመስላችኋል? በሰፊው ተወያዩበት /1፡1-18/

2. በምዕራፍ 1፡12 መሰረት የእግዚአብሔር ልጅነትን ስልጣን ለማግኘት ሁለት መሰረታዊ ነገሮች እንደሚያስፈልጉ ተገልጿል፡፡ እነኚህ ሁለት መሰረታዊ ነገሮች ምን ምን ናቸው ? ብዙ ሰዎች በቀላሉ የሚቀበሉት አንዱ እውነት የትኛው ነው? በቀላሉ የማይቀበሉስ?

3. ከእግዚአብሔር መወለድ ማለት ምን ማለት ነው?/1፡13/ ይህ ክፍል ስለጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በመንፈስ ቅዱስ ሐይል ከድንግል መወለዱን የሚያመለክት ይመስላችኋል? ተወያዩበት

4. የጌታን ክብር ያየነው እንዴት ነው /1፡14/?

5. ‹በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል. . . › ሲል ምን ማለቱ ነው /1፡16/ ይህስ ጸጋ የተሰጠው ለማን ነው ?

6. በ1፡17 ላይ ፀጋና ህግ ተነጻጽረው እናገኛለን ፡፡ ስለዚህ ፀጋ የህግ ተቃራኒ ነው ማለት እንችላለን? በሰፊው ተወያዩበት፡፡

7. በ1፡10 ላይ ዓለም የሚለው ቃል 3 ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ በዚህ ክፍል አለም የሚለው ማንን ለማመልከት ነው ? አለም ጌታን ያላወቀውስ ለምን ይመስላችኋል?

8. ‹ቃልም በእኛ አደረ› ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኋል /1፡14/? /ዘፀ 40፡34-35 ያለውን ክፍል ተመልከቱ/

9. መጥምቁ ዮሐንስ አይሁድ ‹አንተ ማን ነህ› ብለው በተደጋጋሚ ለጠየቁት ጥያቄ ከሰጠው መልስ ምን እንማራለን /1፡19-23/?

10. በዮሐንስ ወንጌል ላይ ጌታ ኢየሱስ ሁለት ጊዜ <u>‹የእግዚብሔር በግ›</u> ተብሎ ተጠቅሷል /1፡29 ፣ 1፡36/፡፡ /በራዕይ መፅሐፍ በብዙ ቦታዎች የታረደው በግ ወይም በጉ ተብሎ ተጠቅሷል / ራዕ 5፡6፣ ራዕ 5፡8፣ ራዕ 5፡12-13፣ ራዕ 6፡1፣ ራዕ 6፡16/፡፡ ይህን አሳብ በዘፀ 12፡1-28 እና ኢሳ 53፡1-12 ካለው ሃሳብ ጋር በማዛመድ ተወያዩበት፡፡

11. በ1፡29 ላይ ‹የአለምን ሃጢአት ለማስወገድና› የሚለው ሃሳብ የሰውን ዘር በሙሉ የሚያድን መሆኑን ለማመልከት የተጠቀሰ ይመስላችኋል /Universal Salvation/?

12. በ1፡40 ላይ ደቀመዛሙርት መጥተው ከጌታ ጋር የዋሉበት ሰአት /አስር ሰአት/ መጠቀሱ ምንን የሚያመለክት ይመስላችኋል? ጌታ ኢየሱስን ለመከተል የወሰናችሁበትን ቀንና ሰአት ታስተውሳላችሁ?

13. ጌታ ኢየሱስ ለተከተሉት ደቀመዛሙርት ‹ምን ትፈልጋላችሁ?› ብሎ መጠየቁ ምን ያስተምረናል /1፡38/? ጌታን የምትከተሉት ለምን እንደሆነ /ወይም ምን ፈልጋችሁ እንደሆነ / በትክክል ታውቃላችሁ? ‹ረቢ ወዴት ትኖራለህ?› የሚለውስ መልስ ምን ያስተምረናል?

14. ናትናኤል ‹ከናዝሬት  መልካም ነገር ሊወጣ ይችላልን?›ማለቱ ምን ያስተምረናል /1፡47/ ? /ናዝሬት በጣም ትንሽና ብዙ ጠቀሜታ የሌላት /insignificant/ መንደር የነበረች ስትሆን በብሉይ ኪዳንም ሆነ በወቅቱ በነበሩ የአይሁድ ፅሁፎች /literatures / በፍፁም ስሟ ያልተጠቀሰ መንደር ነች፡፡/ ፊልጶስ ናትናኤልን መጥተህ እይ በማለቱ ናትናኤል ህይወት ውስጥ ምን ሆነ? ይህስ እኛ ስለጌታ ኢየሱስ ለሰዎች ስለምንሰጠው ምስክርነት ምን ያስተምረናል?

## <u>ለ. ሰባቱ የተመረጡ ተአምራቶች</u>

### <u>ውሃው ወደወይን ጠጅ የተለወጠበት /2፡1-11/</u>

1. ጌታ ኢየሱስ በሰርግ ላይ ሲጋበዝ አክብሮ መገኘቱ ምን ያስተምረናል?

2. ይህ ሰርግ በወቅቱ በነበረው ባህል መሰረት ለአንድ ሳምንት የሚካሄድና የከተማው ህዝብ በሙሉ የሚጋበዝበት ከፍ ያለ ግብዣ ሲሆን በሰርጉ መሐል የወይን ጠጅ ማለቅ ማለት ትልቅ ውርደት ነው፡፡ ማርያም ይህንን ትልቅ ችግር ወደ ኢየሱስ ይዛ መምጣቷ ምን ያስተምረናል? እኛስ በህይወታችን ትልቅ ችግር ሲደርስብን መጀመሪያ የምናደርገው ነገር ምንድነው?

3. በዚህ ውሃውን ወደ  ወይን ጠጅ በመለወጥ ተአምራት ላይ የአገልጋዮቹ ድርሻ ምን ነበር? የአገልጋዮቹ ለጌታ ትእዛዝ የሰጡት ምላሽ ምን ያስተምረናል?

4. ጌታ ኢየሱስ ለመጥመቅ ብዙ ጊዜ የሚፈጀውን ወይን ጠጅ በአጭር ጊዜ ወይን ሳይኖር መጥመቂያ ሳይኖር ምንም ነገር ሳይኖር ከውሃ ብቻ መለወጡ ስለጌታ ኢየሱስ ማንነት ምን ያስተምረናል?

5. ጌታ ይህን ተአምራት ያደረገበት ዋናው ምክንያት ምን ይመስላችኋል /1፡11/?

6. አንዳንድ ሰዎች ይህን ክፍል በመጥቀስ አልኮል መጠጣት ይፈቀዳል ይላሉ መስከር ነው እንጂ የተከለከለው መጠጣት ምንም ችግር የለውም ይላሉ ይህን አሳብ ተወያዩበት

7. ጌታ ኢየሱስ ጊዜዬ ገና አልደረሰም /2፡4/ ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኋል? /የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከቱ 7፡30፣ 8፡20፣ 12፡23፣ 12፡27፣ 13፡1፣ 17፡1/

8. በዚህ የሰርግ ግብዣ ላይ የነበረው የወይን ጠጅ ማለቁና ጌታ ኢየሱስ አዲስና በጣም ጣፋጭ የሆነውን የወይን ጠጅ በተአምራት ማስገኘቱ በወቅቱ ለነበሩት አይሁድ ምን መንፈሳዊ ትርጉም ያለው ይመስላችኋል? በሰፊው ተወያዩበት

**<u>የሹም ልጅ መፈወስ /4፡46-54/</u>**

1. ይህ ሹም ስለጌታ መስማቱ ፣ ችግሩን ወደጌታ ማምጣቱና ጌታም ያለውን ሰምቶና አምኖ መሄዱ እንዲሁም ልጁ የተፈወሰበትን ሰአት መጠየቁ ምን ያስተምረናል? እግዚአብሔር በቃሉ የሚናገረንን ሁልጊዜ አምነንና ተቀብለን ለመጓዝ የምንቸገረው ለምን ይመስላችኋል?

2. ጌታ ኢየሱስ ቃና ዘገሊላ ላይ ሆኖ ቅፍርናሆም ያለውን በሽተኛ ልጅ መፈወሱ ስለጌታ ኢየሱስ ምን ያስተምረናል?

   /ቅፍርናሆን ከቃላ ዘገሊላ እስከ 20 ማይልስ ሊርቅ እንደሚችል ይታመናል/

3. ጌታ ኢየሱስ ይህንን ምልክት /ተአምር/ ያደረገው ለምን ይመስላችኋል /ቁ 48ን በሚገባ ተመልከቱ/?

4. በዮሐንስ ወንጌል ላይ ጌታ ኢየሱስ <u>የተከበረ የአይሁድ መሪ</u> የሆነውን ኒቆዲሞስን /3፡1-21/፣ <u>የተጠላችና የተናቀች</u> <u>የሰማርያ ሴት</u> የሆነችውን /4፡1-42/ እና እንዲሁም በዚህ ክፍል <u>የሮማን መንግስት ሹም</u> ማገልገሉ ስለጌታ ተልእኮ ምን ያስተምረናል?

**<u>ከሰላሳ ስምንት አመት ጀምሮ የታመመው ሰው መፈወስ /5፡1-9/</u>**

1. ጌታ ይህን ሰው ‹ልትድን ትወዳለህ›? ብሎ ሲጠይቀው‹ሰው የለኝም› ብሎ መመለሱ ምን ያስተምረናል/5፡6-7/ ?

2. ይህን ለረጅም ዘመን ማለትም ለሰላሳ ስምንት አመትታ የነበረው ሰው በአንድ ቃል ‹ተነሳና አልጋህን ተሸክመህ ሂድ› ብሎ መፈወሱ ስለጌታ ምን ያስተምረናል?

3. ጌታ ኢየሱስ ሰውየውን ባየው ጊዜ ብዙ ዘመን እንዲህ እንደሆነ <u>አውቆ</u> ሲል ምን ማለት ይመስላችኋል? ብዙውን ጊዜ የእኛን ነገር በተለይ በጸሎት የዘገየብንን ነገር ጌታ በርግጥ እንደሚያውቅ አምኖ መቀበል የሚከብደን ለምን ይመስላችኋል?

**<u>አምስት ሺ ሰዎች መመገቡ /6፡1-15/</u>**

1. በአራቱም ወንጌላት ውስጥ ከ35 በላይ በጌታ የተደረገ ተአምራት ተጠቅሰዋል፡፡ ከነዚህ ተአምራት ውስጥ በ5 እንጀራና በ2 አሳ 5000 መመገቡ በአራቱም ወንጌላት ውስጥ ተጽፎአል፡፡ ይህ ተአምራት በአራቱም ወንጌላት ውስጥ መጠቀሱ ምን ያስተምረናል /ማቴ 14፡13-21፣ ማር 6፡30-44፣ ሉቃስ 9፡10-17/?

2. አምስት እንጀራና ሁለት አሳ ባርኮ አምስት ሺ ሰዎችን አጥግቦ ማትረፉ ጌታ ኢየሱስ ማን መሆኑን ያመለክተናል?

3. በቁጥር 5፡6 ላይ ጌታ ፊሊጶስን <እነዚህ እንዲበሉ እንጀራ ከወዴት እንገዛለን ?>ብሎ ፈተነው ይላል /ዘኁልቁ 11፡13 ተመልከቱ/፡፡ ፊልጶስ ከዚህ ፈተና ምን የሚማር ይመስላችኋል? አንዳንድ ጊዜ ጌታ ሰዎችን ለምን ይፈትናል? እናንተስ ጌታ በህይወታችሁ ፈትኖአችሁ ያውቃል ? /ጌታ ፊልጶስን የጠየቀበት ምክንያት አካባቢውን በደንብ የሚያውቀውና ምግብ ከተገኘ የት ቦታ እንደሚገኝ የሚያውቅ ቢኖር ፊልጶስ ስለሆነ ነው ፊልጶስ ከቤተሳይዳ ማለትም ከቦታው 9 ማይልስ ርቀት ላይ የኖረ ሰው ነው፡፡/

4. ፊልጶስ ጌታ ለጠየቀው ጥያቄ በቀጥታ መልስ የሰጠ ይመስላችኋል /ቁ7/? አንዳንድ ጊዜ ጌታ የሚጠይቀንና የእኛ መልስ ይለያይ ይሆን?

5. ጌታ ደቀመዛሙርቱ ሰዎቹን እንዲቀመጡ አድርጉ ሲል በደቀመዛሙርቱ ውስጥ ምን አሳብ የሚመጣባቸው ይመስላችኋል? ጌታ ተአምራት ከማድረጉ በፊት የእኛን ፍጹም እምነትና መታዘዝ እንደሚፈልግ በሰፊው ተወያዩበት

6. ጌታ ትርፍራፊውን በሙሉ አከማቹ ያለው ለምን ይመስላችኋል /6፡12-13/?

7. ይህን ክፍል ከ2ኛ ነገ 4፡42-44 እና ከኢሳ 25፡6-9 ጋር በማዛመድ ተወያዩበት

8. በአጠቃላይ ጌታ ይህን ተአምራት ያደረገው ለምን ይመስላችኋል?

9. በቁጥር 15 ላይ ኢየሱስን ሊያነግሱት ማሰባቸው ስህተቱ ምን ላይ ይመስላችኋል? ከዚህ ክፍል የህዝቡን አሳብ፣ ሰይጣን በማቴ 4፡1-11 ባለው ክፍል ውስጥ

ጌታን ለማንገስ ካቀረበው አሳብ ጋርና እንዲሁም እግዚአብሔር በዘለአለም አሳቡ በዳንኤል 7፡13-14 ላይ ከተጠቀሰው አሳብ ጋር በማያያዝ የጌታን ንግስና ተወያዩበት

**<u>በባህር ላይ መሄድ / 6፡16-21/</u>**

1. ጌታ ኢየሱስ በባህር ላይ /ያውም በሃይል በሚናወጥ ባህር ላይ/ መሄዱ ስለእርሱ ምን ያስተምረናል? /መዝ /89/፡9 ተመልከቱ/

2. ብርቱ ንፋስ ስለነፈሰ ባህሩ እየተናወጠ ነበር በተጨማሪም ጌታ በባህር ላይ እየሄደ ሲመጣ ደቀመዛሙርት አይተው ፈሩ ይላል /6፡19/ ይህ ጌታ በህይወታችን በሚያስፈራ መንገድ ሊመጣ እንደሚችል ተወያዩበት፡፡

**<u>የአይነስውሩ ሰው መፈወስ /9፡1-41/</u>**

1. ደቀመዛሙርት ጌታን ከጠየቁት ጥያቄና /9፡2/ ጌታም ከሰጣቸው መልስ /9፡3/ ምን እንማራለን? ብዙ ጊዜ የተቸገረ ሰው <u>ስታዩ ምን አድርጎ ይህ ደረሰበት</u> የሚል ነገር ነው ወይስ <u>ምን እንርዳው</u> የሚል ነገር ነው የሚመጣባችሁ? በግልጽነት /Honestly/ ተወያዩበት /የኢዮብን አጽናኞች አስታውሱ/ እንዲሁም ማንኛውም የግለሰብ፣ የህዝብና የአገሮች ችግር የእግዚአብሔር ክብር ለመግለጥና ለእግዚአብሔር ስራ አመቺ እድል /opportunity/ ሊሆን እንደሚችል በሰፊው ተወያዩበት

2. ደቀመዛሙርቱም ሆኑ ፈሪሳውያን ስለዚህ አይነስውር የነበራቸው አመለካከት ምንድነው /9፡2፣ 9፡28፣ 9፡34/? ይህስ ለእኛ ምን ያስተምረናል? በሽታ ሁሉ የሃጢአት ውጤት ይመስላችኋል? ተወያዩበት /ሉቃስ 13፡2-3፣ 2ኛ ቆሮ 12፡7/

3. ለተፈጥሮአዊ ሰው ሞኝነት በሚመስል መንገድ አይኑን በምራቅ ጭቃ ቀብቶ ሂድና ታጠብ ሲለው በሙሉ መታዘዝ ሄዶ የታዘዘውን መፈጸሙ ስለዚህ ሰው ምን ያስተምረናል?

4. ይህ ሰው ሲፈወስ የጎረቤቶቹና የሚያውቁት ሰዎች ምላሽ /Reaction / ምን ነበር /9፡8-12/? ፈሪሳውያን ስለሰንበት ጉዳይ ነው እንጂ ከመወለዱ ጀምሮ እውር የነበረ ሰው አይን መብራትን የመስራት ተአምራት <u>ማየት</u> ያቃታቸው ለምን ይመስላችኋል /9፡39/?

5. አይሁድና ፈሪሳውያን በዚህ ፈውስ ላይ በተደጋጋሚ የጠየቁት <u>አይኖችህ እንዴት ተከፈቱ</u> /9፡10፣ 9፡15፣ 9፡19፣ 9፡21፣ 9፡26/? እንጂ <u>ማን ከፈተልህ</u> ? የሚለው ጥያቄ ላይ አለማተኮራቸው ምን ያስተምረናል? በተጨማሪም ፈሪሳውያን ጌታ

ኢየሱስን ሐጢያተኛ /ቁጥር 24/ እንዲሁም ከወዴት እንደሆነ የማይታወቅ ሰው /ቁጥር 29/ ማለታቸው ስለ እነርሱ ምን ያስተምረናል?

6. ጌታ ይህን ተአምራት ያደረገው ለምን ይመስላችኋል?

7. ከመወለዱ ጀምሮ አይቶ የማያውቀውን ሰው አይን ማብራቱ ስለጌታ ማንነት ምን ያስተምረናል?

8. አንዳንድ ጊዜ በችግርና በመከራ የምናልፍበት ምክንያት ‹የእግዚአብሔር ስራ በእኛ እንዲገለጥ› ሊሆን ይችላል ማለት ነው /9፡3/?

9. ጌታ ኢየሱስ ቀን እና ሌሊት ብሎ ስለጊዜ ሲጠቅስ የትኛውን ጊዜ ማለቱ ነው /9፡4/? ለእኛስ የምንሰራበት ቀንና የማንሰራበት ሌሊት ይኖራል ማለት እንችላለን? ካለስ ምን ማድረግ ይገባናል?

10. ወላጆቹ ያንን ያህል ትልቅ ተአምራት ለልጃቸው ተደርጎ ነገር ግን አይሁድን መፍራታቸው ስለእምነታችን ምን ያስተምረናል /9፡2-,23/?/በዚህ ወቅት ከምኩራብ እንዳይገለሉ ነው የፈሩት በወቅቱ ከምኩራብ መገለል ማለት የህይወትን አቅጣጫ በሙሉ /civil, recreational, legal and religious / የሚነካ ስለሆነ ነው የፈሩት/

11. ጌታ በ9፡41 ላይ ‹ . . . እውሮች ብትሆኑ ሃጢአት ባልሆነባችሁ ነበር አሁን ግን እናያለን ትላላችሁ ኃጢአታችሁም ይኖራል› ሲል ምን ማለቱ ነው?

12. ጌታ በ9፡39 ላይ ‹. . . ወደዚህ አለም ለፍርድ መጣሁ› የሚለውን ሃሳብ በዮሐንስ 3፡17 ካለው ጋር በማዛመድ ተወያዩበት፡፡

**የሞተው መነሳት /11፡1-44/**

1. በ11፡4 ላይ ህመም ለእግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ ለሞት አይደለም ሲል ምን ማለቱ ይመስላችኋል?

2. ጌታ ሰዎችን ለይቶ የሚወደው ለምንድነው /11፡5/?

3. አልአዛር ሞቶ ተቀብሮ እያለ ጌታ ግን ‹ወዳጃችን አልአዛር ተኝቶአል ከእንቅልፉ ላስነሳው እሄዳለሁ› ማለቱ ምን ማለቱ ይመስላችኋል /11፡11/?

4. ጌታ ኢየሱስ አልአዛርን ከማስነሳት ይልቅ ብዙ ጊዜ የፈጀበት ማርያምንና ማርታን ማሳመን መሆኑ ምን ያስተምረናል?

5. በዚህ ክፍል ጌታ እንባውን ማፍሰሱ ምን ያስተምረናል /11፡35/?

6. በዚህ ክፍል ጌታ ሁለት ጊዜ ‹ድንጋዩን አንሱት› ያለው ለምንድነው? በህይወታችን አበቃለት ተስፋ የለውም ያልነው ነገር አለ? ጌታ ድንጋዩን አንሱት ቢለን ምላሻችን ምንድነው?

7. ጌታ ኢየሱስ ይህን ተአምራት ያደረገው ለምን ይመስላችኂል /11፡15፣ 11፡45/?

8. የሞተውን በስሙ ጠርቶ ማስነሳቱ ስለጌታ ኢየሱስ ምን ያስተምረናል?

9. በአልአዛር ከሞት መነሳትና የጌታ ኢየሱስ ከሞት መነሳት መካከል ያለውን ልዩነት ተወያዩበት

10. በ11፡37 ላይ የተጠቀሰው አሳብ ስለሰው ልጆች ምላሽ /reaction/ ምን ያስተምረናል?

11. ከሞተ አራት ቀን እንደሆነው ሁለት ጊዜ መጠቀሱ /11፡17፣ 11፡39/ ምንን ለማመልከት ይመስላችኂል?

12. ጌታ ድረስልን ለሚለው ጥሪ ሁለት ቀን ጨምሮ መቆየቱ ምን ያስተምረናል /11፡6/? አንዳንድ ጊዜ ጌታን ጠርተነው ከዘገየብን በችግራችን ላይ የበለጠ ክብሩን ሊገልጥ እንደሆነ እናስባለን ? ተወያዩበት

13. በቁጥር 9 እና 10 ላይ በቀን የሚመላለስና በሌሊት የሚመላለስ ሲል ምን ማለቱ ነው ?

14. በቁጥር 33 ላይና በቁጥር 38 ላይ ጌታ ኢየሱስ በመንፈሱ ማዘኑን /deeply moved/ ይናገራል፡፡ የዚህ ክፍል የግሪኩ ቃል /embrimaomai/ ትርጉሙ በጉዳዩ በጥልቀትና በሃይል መሰማትን የሚገልጽ ነው፡፡ ይህን ጥልቀት ያለው ሃዘን በሰው ልጆች የመጨረሻ ጠላት በሆነው በሞት ላይ /1ኛቆሮ 15፡26፣ ራዕ 21፡4/ ያለውን ቁጣም ያሳያል፡፡ ስለዚህ ይህን አሳብ በክርስቶስ ከሚገልጠውና በሞት ላይ ስልጣን ባለው በእግዚአብሔር ሃይልና በመጨረሻው ዘመን ከሚገለጠው ከሰው ልጆች ትንሳኤ ጋር በማዛመድ ተወያዩበት፡፡

15. ጌታ ኢየሱስ በቁጥር 43 ላይ ‹አልአዛር ሆይ ወደውጪ ና› ብሎ መጮሁን ከዮሐንስ 1፡3 እና 1፡10 ጋር በማዛመድ ተወያዩበት፡፡

## ሐ. ጌታ ኢየሱስ ‹እኔ ነኝ› /ego eimi/ ያለባቸው ትምህርቶች

### With predicate - እኔ ነኝ ያለባቸው

1. ‹የህይወት እንጀራ እኔ ነኝ› /6፡35/ ሲል ምን ማለቱ ነው?
2. ‹የአለም ብርሃን እኔ ነኝ› /8፡12፣ 9፡5/ ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. ‹እኔ የበጎች በር ነኝ› /10፡7/ ሲል ምን ማለቱ ነው?
4. ‹መልካም እረኛ እኔ ነኝ› /10፡11፣ 10፡14/ ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. ‹ትንሳኤና ህይወት እኔ ነኝ› /11፡25/ ሲል ምን ማለቱ ነው?
6. ‹እኔ መንገድና እውነት ህይወትም ነኝ› /14፡6/ ሲል ምን ማለቱ ነው?
7. ‹እውነተኛ የወይን ግንድ እኔ ነኝ› /15፡1/ ሲል ምን ማለቱ ነው?

- ጌታ ኢየሱስ እኔ ነኝ ያለባቸው ከላይ የተጠቀሱትን በሙሉ በቃላችሁ ያዙአቸው ‹Memorize›

**በፍጹምነት እኔ ነኝ ያለባቸው**

በሚከተሉት ቦታዎች ጌታ ኢየሱስ ‹እኔ ነኝ› ማለቱ ምን ለማመልከት እንደሆነ በብሉይ ኪዳን በዘፀ 3፡14፣ ኢሳ 41፡4፣ አሳ 43፡10፣ ኢሳ 46፡4 ከተጠቀሰው አሳብ ጋር በማዛመድ ተወያዩበት

- 8፡58
- 18፡5-6
- 18፡8
- 4፡26
- 6፡20
- 8፡24
- 8፡28
- 13፡19

## መ. ሰባቱ ሰፊ ንግግሮችና ትምህርቶች

### ከኒቆዲሞስ ጋር የተነጋገረበት /3፡1-21/

1. ፈሪሳዊው ኒቆዲሞስ በሌሊት ወደ ኢየሱስ መምጣቱ ስለ ኒቆዲሞስ ምን ያስተምረናል / 7፡50፣ 19፡39/? መንፈሳዊ ጨለማነትንስ ሊያመለክት የሚችል ይመስላችኋል /9፡4፣ 11፡10፣ 13፡30/ ? ተወያዩበት፡፡

2. በዮሐንስ 3፡3 ላይ ጌታ ኢየሱስ በግልጽ ቋንቋ ወደ እግዚአብሔር መንግስት ለመግባት የሚያስፈልገው ምን እንደሆነ አስተምሯል፡፡ ይህም ዳግመኛ መወለድ ነው፡፡ ስለዚህ ዳግመኛ መወለድ ማለት ምን ማለት ነው? ዳግመኛ የተወለዳችሁት መቼ ነው? በሰፊው ተወያዩበት /1ኛ ዮሐ 2፡9፣ 1ኛ ዮሐ 3፡9፣ 1ኛ ዮሐ 5፡1፣ 1ኛዮሐ 5፡4፣ 1ኛ ዮሐ 5፡18/

3. በዮሐንስ 3፡16 ላይ ያለውን ቃል በቃላችሁ ያዙት /This is the most summary of the gospel in the entire Bible/

4. ‹በማያምን ሰው ላይ አሁን ተፈርዶበታል› /13፡18/ ሲል ምን ማለቱ ነው?

5. ሰዎች የጌታን እውነት የማይቀበሉት፣ የዘለአለም ህይወት የማይቀበሉት ፣ ነጻ የሆነውን ስጦታ የማይቀበሉት ለምንድነው /3፡19-21/ ?

## ከሳምራዊቷ ሴት ጋር የተነጋገረበት /4፡4-26/

1. ጌታ ኢየሱስ በሰማሪያ ሊያልፍ ‹ግን ሆነበት› /4፡4/ ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህስ ምን ያስተምረናል?

2. ጌታ ኢየሱስ በሚያገለግልበት ወቅት አንድ የተከበረ አይሁድ በመንገድ ላይ /Publicly/ ከሴት ጋር መነጋገር ትልቅ ነውር ነው /4፡27/፡፡ ይህን የወቅቱን ባህል አልፎ ከሴት ጋር ያውም በቀን በ6 ሰአት ከተጠላች ከሃጢአተኛ የሰማርያ ሴት ጋር መነጋገሩ ስለጌታ ምን ያስተምረናል

3. በወቅቱ ሴቶች ውሃ የሚቀዱት በጠዋት ወይም በምሽት ነው ይህች ሴት ግን በእኩለ ቀን በጣም ሞቃት በሆነበት ሰአትና ሰው ሁሉ በሚያርፍበት ሰአት ብቻዋን ውሃ ለመቅዳት መምጣቷ ስለ ሴቲቱ ምን ያስተምረናል?

4. ጌታ ኢየሱስ ውሃ አጠጪኝ ብሎ የጀመረው ንግግር ትልቅ ደረጃ ላይ ደርሶ ብዙዎች እንዳመኑበት ከዚህ ክፍል እናነባለን፡፡ ታዲያ ይህ አይነት አቀራረብ ስለምስክርነት ምን ያስተምረናል? በዚህ አመት ውስጥ ለስንት ሰው ጌታ ኢየሱስን መስክራችኋል? ምን አይነት መንገድ ተጠቀማችሁ? በሰፊው ተወያዩበት፡፡

5. በቁጥር 9 ላይ ‹አይሁድ ከሳምራውያን ጋር አይተባበሩም ነበር› የሚለው ቃል በሌላ አባባል ምንም አይነት ነገር አያደርጉም /they have nothing in common/ የሚለውን ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም አይሁድ ሳምራውያንን ንጹህ ያልሆኑ አድርገው ስለሚያዩአቸው ከእነርሱ ጋር መብላትና መጠጣት እንደ መርከስ ይቆጥሩታል፡፡ ጌታ ኢየሱስ ግን ከሴቲቱ ጋር መነጋገር ብቻ ሳይሆን ውሃ ለመጠጣት እንኳን ፈቃደኛ መሆኑ ስለጌታ ምን ያስተምረናል?

6. ጌታ ኢየሱስ ስለ ውሃው ሲናገር ‹የእግዚአብሔር ስጦታ› /4፡10/ ብሎታል፡፡ ይህ አባባል የዘላለም ህይወትን የሚያመለክት ይመስላችኋል? ተወያዩበት /ኤፌ 2፡8 ተመልከቱ/

7. ጌታ ኢየሱስ ‹የህይወት ውሃ ይሰጥሽ ነበረ› ሲል ምን ለማመልከት ይመስላችኋል ?/የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከቱ ዘፍ 26፡19፣ ኢሳ 12፡3 ፣ ኤር 2፡13፣ ህዝ 47፡1-5፣ ዘካ 14፡8፣ ዮሐ 7፡38-39/

8. ጌታ ኢየሱስ ‹እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ለዘላለም አይጠማም› /4፡14/ ሲል ምን ማለቱ ነው? ይህን አባባል የተጠቀመው መንፈሳዊውን ወይስ ስጋውን ለማመልከት ይመስላችኋል? እኔ የምሰጠው ሲልና ራሱ ሰጪ መሆኑን ሲያመለክት መለኮታዊ ስልጣኑን ለማስተማር የፈለገ ይመስላችኋል? ተወያዩበት

9. በቁጥር 15 ላይ ሲቲቱ ጌታን እንዳልተረዳችው /misunderstand/ እናያለን፡፡ ምክንያቱም በቀጥታ /literally/ ስለምድራዊ ውሃ የሚናገር ስለመሰላት ነው፡፡ ዛሬስ በዘመናችን ጌታን በተሳሳተ መንገድ የሚረዱ ሰዎች ያሉ ይመስላችኋል? ተወያዩበት

10. እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ማምለክ ማለት ምን ማለት ነው /4፡20-24/?

11. ጌታ በ4፡35 ላይ ‹. . . አይናችሁን አንሱ አዝመራው እንደነጣ እርሻውን ተመልከቱ › ያለው አባባል ምን ያስተምረናል?

**ከአይሁድ መሪዎች ጋር የተነጋገረበት /5፡10-47/**

1. አይሁድ ሰላሳ ስምንት አመት ሙሉ ታሞ የነበረው ሰው መፈወስ ይልቅ ሰንበት ላይ ማተኮራቸው ለምን ይመስላችኋል? /ብሉይ ኪዳን በሰንበት አልጋን ተሸክሞ መሄድ የተከለከለ መሆኑን በፍጹም አያስተምርም፡፡ ሆኖም ከቃሉ በተጨማሪ አይሁድ ወግ

/tradition/ ስላላቸውና ስለሚከተሉ በዚህ በሚከተሉት ወጋቸው መሰረት በሰንበት ምን መስራት እንዳለበትና እንደሌለበት ተገልጿል /Mishnah, Shabbat 7:2/

2. በ5፡14 ላይ ጌታ ‹ከዚህ የሚብስ እንዳይደርስብህ . . . › ሲል የእግዚአብሔርን የዘላለም ፍርድ ለማመልከት ይመስላችኋል ? በሽታ ሁሉ በሐጢአት ምክንያት የሚመጣ ነው ማለት ይቻላል? ተወያዩበት

3. ጌታ ኢየሱስ በ5፡17 ላይ‹ አባቴ እስከዛሬ ይሰራል እኔም እስከዛሬ እሰራለሁ› ማለቱ አምላክነቱን ለመግለጽ ይመስላችኋል? /ቁጥር 18ን ይመልከቱ/

4. በ5፡19፡23 ባለው ክፍል ውስጥ ስለአብና ወልድ የተገለጸውን ሃሳብ /ጌታ ኢየሱስ ራሱን ከአብ ጋር እያነጻጸረ የተናገረውን/ ተወያዩበት ፡፡ በአጠቃላይ ክፍሉ ስለጌታ ኢየሱስ ምን የሚያስተምር ይመስላችኋል?

5. በ5፡24 ላይ የተጠቀሰው አሳብ እጅግ አስገራሚና ጠቃሚም ነው፡፡ በዚህ ክፍል መሰረት ሰው የዘላለም ህይወት የሚያገኘው ወይም ከሞት ወደ ህይወት የሚሻገረው በምንድነው? የዘላለም ህይወት የሚጀምረው መቼ ነው?

6. በቁጥር 23 ላይ‹ . . . ወልድን የማያከብር አብን አያከብርም › የሚለው ሃሳብ ለአይሁድ እምነት ወይም ለእስልምና እምነት ተከታዮች ምን የሚያስተምራቸው ይመስላችኋል?

7. በቁጥር 25 ላይ <u>ሙታን</u> ሲል ማንን ማለቱ ነው? በህይወት ይኖራሉ ሲልስ ምን ለማመልከት ይመስላችኋል?

8. አንድ ሰው በ5፡29 ያለውን አሳብ ማለትም <u>‹መልካም ያደረጉ</u> ለህይወት ትንሳኤ <u>ክፉም ያደረጉ</u> ለፍርድ ትንሳኤ ይወጣሉና በዚህ አትደነቁ› የሚለውን በመጥቀስ በመጨረሻው ዘመን የሚሰጠው ፍርድ በስራ ነው ብሎ ቢያስተምር ስህተቱ ምን ላይ ይመስላችኋል?

9. በ5፡30-47 ባለው ክፍል ውስጥ ስለጌታ ኢየሱስ የሚመሰክሩ <u>አምስት</u> ምስክሮች ተገልጸዋል፡፡ እነዚህ ምስክሮች ምን ምን ናቸው፡፡ /የሚከተሉትን ጥቅሶች ተመልከቱ ዘዳ17፡6 ፣ ዘዳ 19፡15፣ ዘኖልቅ 35፡30/ እነዚህ ምስክሮች ስለጌታ የሚሰክሩት ምንድነው? ጌታ ኢየሱስ ከአንድ በላይ ምስክር እያለው ሰዎች እርሱን አለመቀበላቸው ምን ያመለክታል?

## ስለህይወት እንጀራ የተነጋገሩበት /6፡22-59/

1. ሰው ጌታ ኢየሱስን መፈለግ ያለበት በዋናነት ለምንድነው? ተአምራት አይቶ ጌታን መከተል ትክክል ሊሆን የሚቻለውስ እንዴት ነው /6፡25-26/?በሰፊው ተወያዩበት፡፡

2. በቁጥር 27 ላይ ጌታ ኢየሱስ የሚጠፋ መብልና የማይጠፋ መብል ሲል ምን ማለቱ ነው? በዚሁ ክፍል ላይ ‹እርሱን እግዚአብሔር አብ አትሞታል› የሚለውስ ማንን ነው ? ምንንስ ለማመልከት ነው?

3. የእግዚአብሔርን ስራ በመስራትና እግዚአብሔር በላከው በኢየሱስ በማመን መካከል ያለው ግንኙነት ምንድነው? በዚህ ክፍል ህዝቡ የእግዚአብሔርን ስራ እንድንሰራ ምን እናድርግ? ብለው በመጠየቃቸው ስለዘላለም ህይወት ትክክለኛ አመለካከት ያላቸው ይመስላችኋል /6፡28-34/

4. ጌታ ኢየሱስ ከሰማይ የሚሰጥ፣ እውነተኛ እንጀራ፣ ለአለም ህይወት የሚሰጥ ሲል ምን ማለቱ ነው /ቁ32 እና 33/? ይህን ጥያቄ እስራኤላውያን በምድረበዳ ጉዞ ከበሉት እንጀራ ጋር በማነጻጸር መልሱ /ዘፀ 16፣ ዘኖልቁ 11/ እንዲሁም ከቁጥር 48-51 ያለውን ሃሳብ ተመልከቱ/

5. በቁጥር 34 ላይ ህዝቡ ከጠየቁት ጥያቄ የጌታን መልእክት አሳብ የተረዱ ይመስላችኋል? በዘመናችን ያሉ የብልጽግና ወንጌል ሰባኪዎች ከነኚህ ሰዎች ጋር የሚመሳሰሉ ይመስላችኋል?

6. በቁጥር 37 እና 44 መሰረት ሰው ወደጌታ ኢየሱስ ሊመጣ የሚችለው እንዴት ነው? /ኤፌ 1፡3-6 እና ሮሜ 9 ተመልከቱ/፡፡ ሰው አንዴ ከዳነ በኋላ የዘላለም ህይወቱን የሚያጣ ይመስላችኋል? ተወያዩበት /5፡37-40/

7. በ6፡41-42 ባለው ክፍል ውስጥ የህዝቡ ማንጎራጎር እስራኤላውያን በሙሴና በአሮን ላይ ካንጎራጎሩት ማንጎራጎር ጋር ተመሳሳይነት ያለው ይመስላችኋል /ዘፀ 16፡8፣ ዘኖልቅ 14፡27፣ መዝ 95፡8-9/? ይህስ ለእኛ ምን ያስተምረናል?

8. በቁጥር 44 ላይ ሊመጣ የሚችል የለም የሚለው የግሪክ ቃል /dynami/ የሚያመለክተው በዚህ አለም የሚኖረ ማንም የሰው ልጅ ወደ ኢየሱስ ሊመጣ የሚችልበት የራሱ የሆነ የሞራልም ሆነ መንፈሳዊ ብቃት እንደሌለው የሚያመለክት አስፈላጊ ቃል ነው፡፡ ስለዚህ ወደክርስቶስ ሊመጣና ፍላጎቱንም አቅሙንም የሚሰጠው እግዚአብሔር መሆኑ ለእኛ ምን ያስተምረናል? በሰፊው ተወያዩበት

9. በቁጥር 52 ላይ አይሁድ ጌታ የተናገረውን በቀጥታ /literally/ በመውሰድ ሲሳሳቱ እናያለን /ዘፍ 9፡4፣ ዘሌ 17፡10-14. 26-27፣ ዘዳ 12፡23-24/፡፡ ነገር ግን ጌታ

**‹የሰውን ልጅ ስጋ <u>ካልበላችሁ</u> ደሙንም <u>ካልጠጣችሁ</u> በራሳችሁ ህይወት የላችሁም ›** /**ቁ** 53/ **ሲል ምን ማለቱ ነው**?